የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 31
ADDIS ABABA, 3rd July, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፫/፪ሺ፲፰

የፌደራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር አዋጅ.....ገጽ ፲፱፸፻፩፻፬

Content

Proclamation No. 1413/2026

The Federal Sport Development and Management Proclamation ….Page 19714

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፫/፪ሺ፲፰ ዓ.ም

የፌደራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር አዋጅ

ማንኛውም ሰው በሚኖርበት፣ በሚሰራበት፣ በሚማርበት እና በሚዝናናበት አካባቢ እንደፍላጎቱና እንደችሎታው በግል፣ በቡድን በተደራጀና ባልተደራጀ መልኩ በአካላዊ እንቅስቃሴ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ጤናማና ንቁ ዜጋ፣ አሸናፊ ሀገር መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የስፖርት ዘርፍንና እምቅ ሃብቶቹን በማልማትና በማስተዋወቅ ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን ሁለንተናዊ ጥቅም ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና ቁሳቁሶች ተገቢውን የአስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት ማህበረሰቡ በስፖርት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍና ተጠቃሚ ለመሆን ያለውን መብት ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

PROCLAMATION NO 1413/2026

THE FEDERAL SPORT DEVELOPMENT AND MANAGEMENT PROCLAMATION

Whereas, it is necessary to make any person participate in sport activities individually or in group in place where he lives, works, learns and entertains according to his needs and skills for active and healthy citizens and winning nation;

Whereas, it is vital to develop and promote the sports sector and its potential resources to increase its contribution in the country overall benefits;

Whereas, it is necessary to ensure the right of the community to participate in and benefit from sports activities by establishing an appropriate management and use system for sports facilities and equipment;

የስፖርት መረጃን በተገቢው በመያዝና ተደራሽ በማድረግ ለዘርፉ ሁለንተናዊ ልማት አስፈላጊውን ሚና እንዲያበረክት በማስፈለጉ፤

የስፖርት ዘርፍ የሚመራበትንና የሚተዳደርበትን ወጥ፣ ፍትሐዊና ግልፅ የአሠራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀፅ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌደራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፫/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ስፖርት" ማለት ማንኛውም ሰው ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ ለመዝናናት፣ አካሉን ለመገንባትና አዕምሮን ለማበልፀግ እንዲሁም አቅሙንና ችሎታውን ለመመዘን በግሉ ወይም በቡድን በተደራጀ ወይም ባልተደራጀ ሁኔታ የሚከናወን እንቅስቃሴ ነው፤

፪/ "ስፖርታዊ እንቅስቃሴ" ማለት ማንኛውም ስፖርታዊ ጨዋታ፣ ውድድር፣ ልምምድና ሥልጠናን ይጨምራል፤

Whereas, it is necessary to make contribute its role for the sectorial development by keeping and making sports information accessible;

Whereas, it is necessary to establish a uniform, fair and transparent procedures by which the sports sector is managed and directed;

NOW TEREFORE, According to Sub-Article (1) of Article 55 the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the following is proclaimed.

PART ONE
General Provisions

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Federal Sport Development and Management Proclamation No 1413/2026".

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Sport"** means an activity that any person performs, individually or in organized or formal or in informal manner, to maintain his health, to build his body, for recreation, to enrich his mind, and to measure his abilities and skills;

2/ **"Sport activity"** means any sporting game, competition and includes practice and training;

፫/ “የስፖርት ሁነት” ማለት ስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ መዝናኛ ፣ ፌስቲቫል፣ ስብሰባ፣ ሴሚናር፣ ሲንፖዚየም፣ ኮንፈረንስ፣ ወርክሾፕን እና ውድድርን ያጠቃልላል፤

3/ "**Sporting event**" means sports activities, sport recreation, festival, meeting, seminar, symposium, conference, workshop and competition;

፬/ “የስፖርት ልማት” ማለት ስፖርትን በዘላቂነትና በሁለንተናዊነት ለማሳደግ የሚከናወን ማንኛውም ተግባር ነው፤

4/ "**Sports Development**" means any activity undertaken to develop sport in a sustainable manner;

፭/ “የስፖርት አስተዳደር” ማለት ስፖርትን በሁለንተናዊ መስክ የመምራት፣ የመደገፍና የመከታተል ሂደት ነው፤

5/ "**Sport management**" means the process of leading, supporting, and monitoring sports by overall aspects;

፮/ “የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ” ማለት ለስፖርታዊ ሁነት ማከናወኛነት እንዲውል የተዘጋጀ ቦታ ነው፤

6/ "**Sports Facilities**" means a place prepared for sporting events;

፯/ “የስፖርት ትጥቅና መሳሪያ” ማለት ስፖርታዊ እንቅስቃሴን ለማከናወን የሚያገለግል ትጥቅ እና መሳሪያ ነው፤

7/ "**Sports Equipment**" means any equipment used to perform sports;

፰/ “የስፖርት ኢንቨስትመንት” ማለት ለስፖርት የሚያገለግል ግብዓት ለማምረትና አገልግሎት ለማቅረብ በባለሃብቱ በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤

8/ "**Sport investment**" means a capital expenditure made by an investor in cash or in kind, or both, to manufacture products and provide services used for sports;

፱/ “አትሌት” ማለት በመደበኛ ስልጠና በመታገዝ በስፖርታዊ ውድድር ወይም ጨዋታ ላይ የሚሳተፍ ሰው ነው፤

9/ "**Athlete**" means a person who participates in sport competition supported by regular training;

፲/ “ብሔራዊ ቡድን” ማለት ሀገርን በመወከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ስፖርታዊ ውድድሮች ወይም ጨዋታዎች ላይ የሚሳተፍ ስብስብ ነው፤

10/ "**National team**" means a body that participates in international sport competition and game representing the country;

፲፩/ “የስፖርት ክለብ” ማለት በአንድ የስፖርት አይነት ተደራጅቶ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ቡድን ነው፤

11/ "**Sports club**" means a team organized in a specific type of sport to engages in sporting activities;

፲፪/ "የስፖርት ባለሙያ" ማለት በስፖርት ሙያ መስክ በመሰልጠን እና ባለው ክህሎት ለመስራት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው ሰው ነው፤

12/ **"Sports professional"** means a person trained in sports and acquired qualification of competence to work by his skill in the field;

፲፫/ "የፌደራል የስፖርት ማህበር" ማለት አንድን የስፖርት ዓይነት ወይም የተለያዩ የስፖርት ዓይነቶችን በአገሪቱ ለማስፋፋትና ለመምራት በሚኒስቴሩ ተመዝግቦ ፈቃድ ያገኘ አደረጃጀት ሆኖ ፌደሬሽኖችን እና ኦሎምፒኮችን ማለት ነው፤

13/ **"Federal Sports Association"** means an organization registered and licensed by the Ministry to expand and lead a specific or various types of sports in the country including Federations and Olympics;

፲፬/ "አለም አቀፍ ውድድር ወይም ጨዋታ" ማለት በሀገራት፣ በክፍለ አህጉር፣ በአህጉር ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ የሚከናወን የስፖርት ውድድር ወይም ጨዋታ ነው፤

14/ **"International Competition or Game"** means any sport competition or game to be conducted among states, at regional, continental or international level;

፲፭/ "አለም አቀፍ ስፖርት ማህበር" ማለት በስፖርት አይነት በአለም አቀፍ ደረጃ የተደራጀ ማህበር ነው፤

15/ **"International Sport Association"** means any sport association organized on specific sport type at International level;

፲፮/ "የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋም" ማለት ተተኪ አትሌቶችን ወይም የስፖርት ባለሙያ ለማፍራት የሚቋቋም ኢንስቲትዩት፣ አካዳሚ ወይም ማዕከል ነው፤

16/ **"Sports Training Institute"** means an academy or center or institute established to produce best Athletes and sport professionals;

፲፯/ **“ስፖርት ንግድ”** ማለት የስፖርት ሁነት ማዘጋጀት፣ ተተኪና ውጤታማ ስፖርተኞች በማፍራት ማዘዋወር፣ በክለብና በአትሌቶች ዝውውር መሰማራት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ማስተዳደርና ማስፋፋት፣ የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎች ማምረት ወይም ከውጭ ሀገር ማስገባት ወይም ማከፋፈል፣ የጂምናዚየም አገልግሎቶችን መስጠት፣ በዘርፉ ማማከር፣ ማሰልጠን እና የምርምር ስራዎችን የማከናወን አገልግሎቶችን ያካትታል፤

17/ **"Sports -related Business"** means the preparation of sports events, the production and transfer of substitute and elite Athlete, the transfer of clubs and Athletes, the management and expansion of sports facilities, the production or importation of sports equipment, the distribution of sports equipment, the provision of gymnasium services, consultation service, It includes conducting research;

፲፰/ **“አበረታች ቅመሞች”** ማለት በዓለም አቀፍ የፀረ አበረታች ቅመሞች ህግጋት ለአትሌት የተከለከለ ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም ዘዴ ነው፤

18/ **"Doping"** means a substance or method prohibited by the International Anti-Doping rules for Athletes;

፲፱/ **“የመሰናዶ ስራ”** ማለት ማንኛውም ሰው ለደንበኞች አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የሚያከናውነው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን የመገንባት ወይም ሌላ ግንባታን ወደ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራነት የመለወጥ እና አስፈላጊ የስፖርት ትጥቆችንና መሣሪያዎችን የማሟላት ሂደት ነው፤

19/ **"Preparatory Work"** means the process of constructing a sport facility or converting another construction to a sport facility and the acquisition of the required sport wears and equipment’s carried out by any person prior to the commencement of providing services to customers;

፳/ **“የአትሌት ማናጀር ወይም ወኪል”** ማለት የአትሌቱን የስልጠና ስርዓት በመደገፍ በዓለም አቀፍ ውድድር እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ሰው ነው፤

20/ **"Athlete Manager or Agent"** means any person that facilitates the participate of Athlete at International sport events;

፳፩/ **“ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር”** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

21/ **"Ministry or Minister"** means the Ministry of Culture and Sports or Minister, respectively;

፳፪/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

22/ "**Region**" means any region established in accordance with Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

፳፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤

23/ "**Person**" means a physical or juridical person;

፳፬/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴት ጾታን ይጨምራል።

24/ Any expression in the Masculine gender includes the Feminine Gender.

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

3. <u>Scope of Application</u>

፩/ ይህ አዋጅ በፌደራል ደረጃ በሚከናወኑ ማንኛውም የስፖርት ልማት እና አስተዳደር ስራዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

1/ This Proclamation is applicable on any sports development and management activities at Federal level.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደርን የተመለከቱ ድንጋጌዎች በመላው ሀገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the provisions concerning the management of sports facilities shall apply throughout the country.

፬. <u>የስፖርት መርሆች</u>

4. <u>Sports Principles</u>

ማንኛውም የስፖርት ልማት እና አስተዳደር በሚከተሉት መርሖዎች ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡-

Any sport development and management shall respect the following principles:

፩/ የስፖርት ተደራሽነት፤

1/ Access to sports;

፪/ በስፖርት ሁለንተናዊ መስተጋብር፤

2/ Overall interaction through sports;

፫/ የዜጎች ተሳትፎና ተወዳዳሪነት፤

3/ Participation and competitiveness of citizens;

፬/ አጋርነትና ቅንጅታዊ አሰራር፤

4/ Coordination and partnership;

፭/ ፍትሐዊነት እና አካታችነት፤

5/ Fairness and inclusiveness;

፮/ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት፤

6/ Transparency and accountability;

ክፍል ሁለት

የስፖርት ተቋማትን ስለማቋቋምና ስለማስተዳደር

ንኡስ ክፍል አንድ

የፌደራል የስፖርት ምክር ቤት ስለማቋቋም

፭. መቋቋም

የፌደራል የስፖርት ምክር ቤት ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፮. የምክር ቤቱ ዓላማ

በአገሪቱ የስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የአሠራር ማነቆዎችን በባለድርሻ አካላት ቅንጅት በመፍታት የስፖርት ልማትን እና ውጤታማ አስተዳደርን ማረጋገጥ ነው።

፯. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የስፖርት መሰረተ ልማት ስለሚስፋፋበት ሁኔታ ይመክራል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

፪/ ስፖርት ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው በሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

፫/ ስፖርት በሃገራዊ የትምህርት ሥርዓት ተካቶ ስለሚለማበትና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ስለሚደገፍበት አግባብ ይመክራል፣ ተገቢውን አቅጣጫ ይሰጣል፣

፬/ ሌሎች ከዓላማው ጋር በሚዛመዱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ አቅጣጫ ይሰጣል።

PART TWO

The Establishment and Management of Sports Institutions

Sub-Section One

The Establishment of the Federal Sport Council

5. Establishment

The Federal Sport Council hereinafter referred to as "**the Council**" is hereby established.

6. Purpose of the Council

It is to ensure the sport development by coordinating stakeholders to solve operational obstacles in the country's sports sector.

7. Powers and Functions of the Council

The Council shall have the following powers and functions:

1/ Discusses and sets direction on the expansion of sports infrastructure;

2/ Discusses and sets direction the on the expansion of community based sport;

3/ Advises and gives direction on the integration of sport in the national educational system and the support of modern technology for the sector;

4/ Advises and gives direction on other issues related to the objectives.

፰. የምክር ቤቱ አባላት

፩/ ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትሩ ---------- ሰብሳቢ፤

ለ) ሚኒስትሩ---------- ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ) የሚኒስቴሩ የስፖርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ---------- ጸሀፊ፤

መ) አግባብነት ያላቸው የፌደራል መንግስት አስፈጻሚ ተቋማት---------- አባላት፤

ሠ) የክልል የስፖርት ምክር ቤት ሰብሳቢዎች---------- አባላት፤

ረ) የክልል የስፖርት አደረጃጀት የበላይ ኃላፊዎች ---------- አባላት፤

ሰ) የፌደራል ስፖርት ማህበራት ፕሬዚዳንቶች ---------- አባላት፤

ሸ) የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ------ አባል፤

ቀ) የኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዚዳንት…….. አባል፤

፪/ የ ፌደራል መንግስት አስፈጻሚ ተቋማት ዝርዝር በሚኒስቴሩ አቅራቢነት በሰብሳቢው ይሰየማሉ፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የምክር ቤቱ ሰብሳቢ እንደአስፈላጊነቱ ለስፖርት ዘርፍ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ታዋቂ ግለሰቦችን ወይም ባለሙያዎችን በስብሰባው እንዲሳተፉ ሊጋብዝ ይችላል፡፡

8. Members of the Council

1/ The Counsel shall have the following members:

a) The Prime Minister…… ……Chairperson;

b) The Minister…… ……...Deputy Chairperson;

c) The State Minister of Sports Development Sector of the Ministry…….Secretary;

d) Relevant Federal Government executive organs……..Members;

e) Chairpersons of Regional Sport Councils……... Members;

f) Heads of Regional Government Sports structure……Members;

g) Presidents of Federal Sports Associations……. Members;

h) President of the Confederation of Ethiopian Trade Unions…… ……Member;

i) President of Ethiopian Sport's Journalists Association…… ……..…. Member;

2/ The chairperson, upon the recommendation of the Ministry, assigns the Federal Government executive organs as members;

3/ Notwithstanding the provisions of sub-Article (1) of this Article, the Chairperson of the Council may, as necessary, invite eminent individuals or experts who have contributed to the sports sector to participate in the meeting.

፱. የምክር ቤቱ ስብሰባ

፩/ ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ድምጽ ወሳኝ ይሆናል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

ንኡስ ክፍል ሁለት

የፌደራል የስፖርት ማህበራት አስተዳደር

፲. የፌደራል ስፖርት ማህበር የቅድመ ምዝገባ መስፈርት

የፌደራል ስፖርት ማህበር እውቅና ለማግኘት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

፩/ ከሃገሪቱ ክልሎች ቢያንስ ከግማሽ በላይ በሆኑት የተመዘገቡና እውቅና ያገኙ የክልል ስፖርት ማህበራትን በአባልነት ያካተተ፤

፪/ የአለም ዓቀፍ የስፖርት ማህበራትንና የሀገራችንን የስፖርት ህጎች ያከበረ የመተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ በጠቅላላ ጉባዔው የፀደቀ ሰነድ ማቅረብ፤

9. Meeting of the Council

1/ The Council shall meet once in a year; provided, however, that it may meet at any time at the call of the chairperson us required.

2/ The presence of more than half of the members of the Council shall constitute quorum.

3/ The Council shall pass decisions through majority votes; and in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this article, the Council may adopt its own rules of procedures.

Sub-Section Two

Management of Federal Sports Associations

10. Pre-registration Requirements of Federal Sports Association

The Federal Sports Association shall meet the following criteria to obtain recognition:

1/ Comprising regional sports associations as members registered and recognized in at least more than half of the regions of the Country;

2/ To submit by laws prepared in accordance with international sport associations laws and national sport laws and approved by general assembly;

፫/ በስፖርት ባህርያቸው ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ማሟላት የማይችሉ የፌደራል የስፖርት ማህበራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገውን መስፈርት ማሟላት አለባቸው፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሰረት ተገቢውን መስፈርት ላሟላ የፌደራል ስፖርት ማህበር የእውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

3/ Federal sport associations, that are unable to satisfy criteria set in Sub Article (1) of this Article due to the inherent nature of the sport, shall satisfy the Sub-Article (2) of this Article requirement.

4/ The Ministry shall provide recognition certificate for federal sport association that meet necessary requirements set in this Article.

፲፩. <u>የፌደራል የስፖርት ማህበራት ምዝገባ</u>

11. <u>Registration of Federal Sports Associations</u>

፩/ ማንኛውም የፌደራል የስፖርት ማህበር ከዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበር የአባልነት እውቅና ማግኘት ይኖርበታል፡፡

1/ Any federal sports association shall acquire member ship recognition from International sport association for registration.

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተቀመጠው ድንጋጌ በባህል ስፖርት በተደራጀ የፌደራል የስፖርት ማህበራት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

2/ The expression stipulated in Sub-Article (1) article 11 of this Proclamation shall not apply on Cultural sports associations.

፫/ ሚኒስቴሩ የፌደራል ስፖርት ማህበራትን መቋቋም፣ ምዝገባ እና የአስተዳደር ስርዓት በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

3/ The establishment, registration and management procedure of federal sport association shall be detained by the Directive to be issued by Ministry.

፲፪. <u>የፌደራል ስፖርት ማህበር አቋም</u>

12. <u>Structure of Federal Sport Association</u>

፩/ የፌደራል የስፖርት ማህበር አቋም በአለም አቀፍ የስፖርት ማህበር ህግ መሰረት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

1/ The structure of Federal Sports Association is determined by the Directives to be issued by the Ministry in accordance with the laws of International Sports Association.

፪/ የፌዴራል ስፖርት ማህበር የምርጫ ሂደትን፣ የተመራጮች የስራ ዘመን ቆይታ፣ የሰው ሀይል አወቃቀር፣ የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀምን እና የኦዲት ስርዓትን በሚመለከት ስፖርት ማህበሩ በሚያወጣው መተዳደሪያ ደንብ መወሰን አለበት፡፡

2/ The Federal Sports Association shall determine the election process, term of office of elected officials, human resource structure, resource mobilization and utilization, and auditing system by their laws.

፲፫. <u>የፌደራል ስፖርት ማህበር ተግባርና ሓላፊነት</u>

የፌደራል ስፖርት ማህበር የሚከተሉት ተግባርና ሓላፊነቶች ይኖሩታል፡-

13. <u>Duties and Responsibilities of the Federal Sports Association</u>

The Federal Sports Association shall have the following duties and responsibilities:

፩/ በተሰማራበት የስፖርት ዓይነት ስፖርትን ያስፋፋል፣ ያለማል፣ የማህበረሰብ ስፖርት ይደግፋል፣

1/ Expands and develops sport on which it engages in, fosters community sport;

፪/ ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ታዳጊ ወጣቶች በመመልመል ስልጠና ይሰጣል፣

2/ Recruits and trains especially talented young people;

፫/ ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ይገነባል፣ ያስፋፋል፣

3/ Builds and expands standard sports facilities;

፬/ በተሰማራበት የስፖርት ዓይነት ለሚሰሩ የስፖርት ባለሙያዎች ተከታታይና ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፣

4/ Performs continuous capacity building activities for sports professionals working in the type of sport they are engaged in;

፭/ በተሰማራበት ስፖርት ዓይነት ለሚቋቋም ስፖርት ክለብ ዝርዝር የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

5/ Issues detail procedure for sport clubs established on sport it engages in and follows its implementation;

፮/ በዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበር የወጡ ህግጋትን፣ አገር ዓቀፍ የስፖርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ፕሮግራም፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲታወቁ፣ እንዲከበሩና እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

6/ Makes the promotion, Respects and ensures the implementation of the rules issued by the International Sports Association, national sports policies, strategies, programs, laws, Regulations, and Directives;

፯/ የፀረ አበረታች ቅመሞች ህግን ያከብራል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ ተገቢውን አሰራር ይዘረጋል፣

፰/ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ስፖርታዊ ሁነቶች ሀገሪቱን ይወክላል፣

፱/ ተግባራቱን ለማከናወን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል።

፲፬. <u>ስለክትትል እና ግምገማ</u>

፩/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር የስራ አፈፃፀምና የፋይናንስ አጠቃቀምን አስመልክቶ በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

፪/ ሚኒስቴሩ የፌደራል ስፖርት ማህበራት ስራቸውን ህግን ተከትሎ ማከናወናቸውን ክትትል ያደርጋል።

፫/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር ሚኒስቴሩ ለሚያከናውነው ክትትልና ቁጥጥር ተገቢውን መረጃ በመስጠት መተባበር ይኖርበታል።

፬/ ሚኒስቴሩ በክትትሉ ውጤት መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

<u>ንኡስ ክፍል ሦስት</u>
<u>ስለ ስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት</u>

፲፭. <u>የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት ስለማቋቋም</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ተገቢውን መስፈርት በማሟላት የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋምን ማቋቋም ይችላል።

7/ Respects the anti-doping laws; follows and controls its implementation, creates awareness on doping and extends its working procedure;

8/ Represents the country on international sport events;

9/ Liaises with relevant parties to carry out its tasks.

14. <u>Monitoring and Evaluation</u>

1/ Every federal sports association shall submit its quarterly performance and financial report to the Ministry.

2/ The Ministry monitors federal sports associations to ensure the proper performance of their duties.

3/ Any federal sports association shall cooperate by giving appropriate information to the experts of monitoring and control to be sent from the Ministry.

4/ The Ministry shall take the necessary measures based on the results of the monitoring.

<u>Sub-Section Three</u>
<u>About sport Training Institutions</u>

15. <u>Establishment of Sport Training Institutions</u>

1/ Any person engaged in the field of sports can establish sports training institute that provides training in various types of sports.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፩) መሰረት የሚቋቋም የማሰልጠኛ ተቋም በሚመለከተው የመንግስት ተቋም ህጋዊ ምዝገባና ዕውቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) ህጋዊ የመመስረቻ ሰነድና የመተዳደሪያ ደንብ፤

ለ) በሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም የፀደቀ የማሰልጠኛ ማንዋል፤

ሐ) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው ባለሙያዎችና አሰልጣኞች፤

መ) ስልጠና የሚሰጥበት የስፖርት ዓይነት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ፣ ቁሳቁስና ጽህፈት ቤት ያሟላ፤

ሠ) የአሠራር ሥርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ያለው፤

ረ) ህጋዊ የገቢ ምንጭ ያለው፤

፫/ ሚኒስቴሩ ስለ ስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት ዝርዝር መስፈርትና የስልጠና ስርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

፲፮. ስለ ስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት አቋም

፩/ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት እንደሚቋቋሙበት ደረጃና እንደሚሰጡት የስልጠና ዓይነት አደረጃጀት ይኖራቸዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት የሚከተሉት ጥቅል አደረጃጀቶች ይኖሯቸዋል፡-

2/ Any training institution established in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall meet the following requirements to obtain legal registration and recognition by the relevant Government institution:

a) An article of association and memorandum of association;

b) Curriculum approved by the relevant Government institution;

c) Coaches who have received appropriate training and have relevant certificate of professional competence;

d) Adequate sports facilities, materials and offices for the type of sport for which training is provided;

e) Having Work procedure and institutional structure.

f) Having a legitimate source of income;

3/ The Ministry shall issue Directive on training system and detailed standard of training institutions.

16. Structure of sport Training Institutions

1/ The sports training institutions established at the federal level may have structure on the basis of their level and training type.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, sports training institutions shall have the following structure:

ሀ) የአስተዳዳር ቦርድ፤

ለ) ዋና ስራ አስፈጻሚ፤ እና

መ) አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

፲፯. <u>የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባርና ሓላፊነት</u>

ማንኛውም የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋም የሚከተሉት ተግባርና ሓላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ ተሰጥዖ ያላቸው ታዳጊዎችንና ወጣቶችን መልምሎ በመቀበል ያሰለጥናል፤ወደ ተለያዩ የስፖርት ክለቦች የሚሸጋገሩበትን የአሰራር መመሪያ በማውጣት ይተገብራል፤

፪/ የሰልጣኞችን የምልመላ መስፈርቶች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫/ የአጫጭርና የመካከለኛ ወይም የረጅም ጊዜ ስልጠና ፕሮግራሞችን በመቅረፅ በተሰማራበት ዘርፍ ለሚሠሩ ባለሙያዎችና አመራሮች ስልጠና ይሰጣል፤

፬/ አግባብነት ያላቸው ስልቶችን በመጠቀም የሰልጣኞቹን ብቃት ይመዝናል፤

፭/ ለሚሰጠው ስልጠና አግባብነት ያለው የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፮/ የሀገር ውስጥ እና ውጭ ሀገር ሰልጣኞችን እና አትሌቶችን በህጋዊ መንገድ በመቀበል ስልጠና ይሰጣል፤

፯/ የአሰልጣኞችና ሰልጣኞችን ስነ ምግባር ይከታተላል፤

፰/ በአበረታች ቅመሞች ዙሪያ በየደረጃው ተከታታይ ስልጠና ይሰጣል፤

a) Board of Directors;

b) Chief Executive Officer ; and

c) The necessary Personnel.

17. <u>Duties and Responsibilities of sport Training Institutions</u>

Any sport training institution shall have the following duties and responsibilities:

1/ Recruits and trains talented kids and youth; and may issue Directive on the transfer of those Athletes to the pertinent bodies engaged in the sport development;

2/ Develops and Implements talent identification and selection criteria for trainees;

3/ Designs short, medium or long-term training programs and providing training to the experts and leaders of the sector;

4/ Evaluates the performance of the trainees by participating in the competition organized by the training institutes of the sector;

5/ Provides appropriate certification for the training provided;

6/ Receives domestic and foreign trainees and Athletes legally and provides training;

7/ Follows the ethics of trainees and coach;

8/ Creates awareness on anti-doping rules;

፱/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣ ሌሎች የገቢ ምንጮችን በመፍጠር ይተገብራል፤

፲/ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፤

፲፩/ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተቋማት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል።

ክፍል ሦስት

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደር

፲፰. የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች አስተዳደር

፩/ የስፖርት ማዘውተሪያ ያስገነባ ሰው ማዘውተሪያውን በባለይዞታነት ያስተዳድራል።

፪/ ሚኒስቴሩ ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን የሚያስተናግድ ማዘውተሪያ ሥፍራ እንዳስፈላጊነቱ ሊገነባ ይችላል።

፫/ በፌደራል ደረጃ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚለሙበት አግባብ እና የሚተዳደሩበት ሁኔታ በደንብ ይወሰናል።

፲፱. የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች አመዳደብ

፩/ ሚኒስቴሩ የዓለም አቀፍ የስፖርት ማህበራት መስፈርትን ተከትሎ የማዘውተሪያ ስፍራ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከደረጃ አንድ እስከ አራት ይመድባል።

፪/ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ በተቀመጠለት ስታንዳርድ መሠረት ለታቀደለት አገልግሎት ብቁ የሚያደርጉትን መሠረታዊ መሥፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት።

፫/ ሚኒስቴሩ የማዘውተሪያ ስፍራዎችን የደረጃ ምደባ መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፣ ተደራሽ ያደርጋል።

9/ Collects reasonable service fee for services rendered; creates other sources of income;

10/ Performs other related activities to achieve its objectives;

11/ Establishes relations with local and foreign institutions that have the same purpose.

PART THREE

Sports Facility Management

18. Management of Sports Facilities

1/ Any person that builds the sports facility manages it as a possessor.

2/ The Ministry may build sport facilities that host international sports events.

3/ The development and manage of federal sport facilities is determined by Regulation to be issued by Council of Ministers.

19. Classification of Sports Facilities

1/ The Ministry, following the criteria of international sport associations, prepare the standard; and classify sports facilities from level one to level four.

2/ Any sports facilities shall meet the basic requirements of the intended purpose according to the set standards.

3/ The Ministry organize and maintain a record of the classification of sports facilities and make it accessible.

፬/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የደረጃ ምደባ ስልጣኑን ለክልል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

4/ The Ministry, when it deems necessary, may delegate its power of classification to the region.

፳. <u>ለመሰናዶ ስራ ፈቃድ ስለመስጠት</u>

20. <u>Grant of Permit</u>

፩/ የመሰናዶ ስራ ለማከናወን ሚኒስቴሩ ከደረጃ አንድ እስከ ሶስት ለሚመድባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ፈቃድ ይሰጣል፡፡

1/ The Ministry gives permit for sports facilities classified as level one up to three.

፪/ አግባብነት ያለው የክልል አካል በደረጃ አራት እና ለሌሎች የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2/ The appropriate regional body gives permit for sports facilities classified as level four and other.

፫/ ሚኒስቴሩ እንዳስፈላጊነቱ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) ለተቀመጡት ደረጃዎች ፈቃድ በክልል እንዲሰጥ ሊወክል ይችላል፡፡

3/ The Ministry may, as may be necessary, delegate to the region to issue permits for the standards set forth in Sub-Article (1) of this Article.

፳፩. <u>ስለማመልከቻ አቀራረብ</u>

21. <u>Submission of Application</u>

፩/ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ማቋቋምና አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ፈቃድ እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ወይም በህግ ስልጣን ላለው የክልል ተቋም ፈቃድ መጠየቅ አለበት፡፡

1/ Anyone who seeks to establish a sports facility and provide services shall apply to the Ministry or relevant regional organ for a permit before starting construction.

፪/ አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር ዝርዝር የመነሻ ሃሳብ፣ የማዘውተሪያ ስፍራውን ፕላን እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ The applicant must attach a detailed initial proposal, site plan and other necessary documents to the application.

፫/ አመልካቹ የመሰናዶ ስራውን ሲያጠናቅቅ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት አለበት፡፡

3/ Upon completion of the preparatory work, the applicant shall apply for a certificate of competence.

፳፪. ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም በህግ ስልጣን የተሰጠው የክልል አካል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ሲያምንበት ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የመሰናዶ ሥራ ለመጀመር የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፣

ለ) አመልካቹ የመሰናዶ ሥራውን ሲያጠናቅቅ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራው በፕላኑ መሠረት ደረጃውን ጠብቆ የተሰናዳ መሆኑን በማረጋገጠ ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በሚኒስቴሩ ለሚሰጥ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አግባብ ባለው የክልል አካል ለሚሰጥ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ መጠን በክልሉ ይወሰናል፡፡

22. Issuance of Permit and Certificate of Competence

1/ The Ministry or the relevant regional organ shall:

a) Issue permit to an applicant to commence preparatory work where, upon examining the application summited to under article 21 of this proclamation, it is convinced that the sport facility meet the standard and upon payment of the fee;

b) Issue a certificate of competence to the applicant upon payment of the fee by verifying that the preparatory work of the sport facility is completed in accordance with its standard plan.

2/ The fees to be charged for permits and certificates of competence to issued by the Ministry in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be determined by Regulation to be issued by Council of Ministers.

3/ According to Sub-Article (1) of this Article, the amount of service fee required for the permit and certificate of competence issued by the appropriate regional body is determined by the region.

፳፫. ስለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አጠቃቀም

፩/ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ስፖርታዊ ሁነቶችን በህግ እንዲከናወኑ ለተፈቀዱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁነቶች ለማስተናገድ፣ የኦሎምፒክ መርሆችን በመከተል ለስፖርቱ ልማት የሚውሉ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራትን ለማከናወን ሊውሉ ይችላሉ፡፡

፪/ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የነበላ የትምህርት ወይም ሌላ ተቋም ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሠረት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ተገቢውን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተመጣጣኝ ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የመንግስትና የህዝብ የማዘውተሪያ ስፍራ ለታዳጊዎች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለሴቶች ስፖርት ያለክፍያ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

23. Use of Sports Facilities

1/ Sports facilities are used to host sporting events, social and economic events permitted by law, and to perform various income-generating activities for the development of sports following Olympic principles.

2/ Any educational or other institution that has built a sports venue should provide services to the community by designing appropriate work procedures.

3/ According to Sub-Articles (1) and (2) of this Article, sports facilities may, by designing appropriate work procedure, request a reasonable fee for the services they render.

4/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (3) of this Article, any Governmental or public sport facility shall provide service for youth, persons with disabilities, and women's free of charge.

፳፬. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከልሎ ስለመያዝ

፩/ ማንኛውም በህግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም፡-

ሀ) ለስፖርት ማዘውተሪያነት የሚውሉ ስፍራዎችን በገጠር ቀበሌ እንደ ህዝቡ አሰፋፈር እና በከተማ መሪ ፕላን መሠረት ከልሎ መያዝ አለበት፤

24. Reserving Areas for Sports Facilities

1/ Any legally empowered organ shall:

a) Reserve places used for sports in rural areas according to the population settlement or master plan in urban center;

ለ) እንደአካባቢው ሁኔታ በህብረተሰቡ የሚዘወተሩ የባህል ስፖርቶችን በማጥናት ለባህል ስፖርት ጨዋታዎች የሚያገለግሉ ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከልሎ መያዝ ይኖርበታል፤

ሐ) በመሪ ፕላኑ ወይም እንደ ህዝቡ አሰፋፈር የተከለሉትን የማዘውተሪያ ስፍራዎች ከሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መያዝ አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በመሪ ማስተር ፕላን ወይም እንደ ህዝቡ አሰፋፈር ስለ መከለላቸው ይከታተላል፣ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

፳፭. <u>የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ስለማልማት</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ መሰረት የተከለለ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ እንደማዘውተሪያው ዓይነት የሚያስፈልጉ ደረጃቸውን ያሟሉ የስፖርት ቁሳቁሶችን አሟልቶ መገንባት አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እና ተስማሚ መሆን አለበት፡፡

b) Study the popular cultural sports of the community and protect the entertainment areas used for cultural sports games;

c) Hold the possession by title deed of the reserved areas in rural or incorporated areas in the master plan in urban center from the relevant body.

2/ The Ministry, according to this Article, follows up and provide professional support regarding the inclusion of sports facilities in the master plan or reservation of areas in rural.

25. <u>Development of Sports Facilities</u>

1/ Any sports facilities reserved according to Article 24 of this Proclamation, on its type, shall be constructed satisfying the basic standards of sport equipment's.

2/ Any sports facilities must be accessible and suitable for persons with disabilities.

ክፍል አራት

የአትሌቶች እና የስፖርት ባለሙያዎች አስተዳደር

ንዑስ ክፍል አንድ

የአትሌቶች አስተዳደር ሥርዓት

፳፮. የአትሌቶች ምዝገባ

፩/ ማንኛውም በሀገርና በአለም ዓቀፍ ስፖርታዊ ሁነት የሚሳተፍ አትሌት በቅድሚያ በሚመለከተው ፌደራል ስፖርት ማህበር መመዝገብ አለበት፡፡

፪/ የሚመለከተው ስፖርት ማህበር የአመዘጋገብ ስርዓት የሚመራበትን መመሪያ በማዘጋጀት ይተገብራል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ መሰረት ያልተመዘገበ አትሌት በማንኛውም አገር አቀፍ እና አገሪቱን በመወከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄድ ስፖርታዊ ሁነቶች ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

፳፯. የሀገር ውስጥ አትሌቶች ዝውውርና ቅጥር አስተዳደር

፩/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር አትሌት እንደየዕድሜ ደረጃውና የስፖርት ዓይነት ስለሚቀጠርበትና ስለሚዛወርበት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ የማንኛውም አትሌት የዝውውር ወይም የቅጥር የውል ስምምነት በሚመለከተው የፌደራል የስፖርት ማህበር መጽደቅ አለበት፡፡

፳፰. የውጭ ሀገር አትሌቶችን ስለመቅጠር

፩/ ማንኛውም የስፖርት ክለብ ከሚኒስቴሩ በሚያገኘው ፈቃድ መሰረት የውጭ ሀገር አትሌቶችን መቅጠር ይችላል፤

PART FOUR

Management of Athletes and Sports Professional

Sub-Section One

Athlete Management

26. Athletes Registration

1/ An Athlete who participates in any national or international sports event shall first be registered with the relevant federal sports association.

2/ Any federal sports association shall prepare and implement the guidelines governing the registration system.

3/ In accordance with this Article, unregistered Athlete cannot participate at any national level and international sporting events by representing the country.

27. Local Athletes Transfer and Employment Administration

1/ Any federal sports association issues detailed guidelines on the employment and transfer of Athletes, According to their age level and type of sport.

2/ The contract of the employer and the Athlete must be approved by the relevant federal sports association.

28. Employment of Foreign Athletes

1/ Any sports club, based on the permission given from the Ministry, may hire foreign Athletes;

፪/ የውጭ ሀገር አትሌቶች የክፍያ ስርዓትና የቅጥር መስፈርት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፡፡

2/ The payment system and employment criteria for foreign Athletes will be implemented according to the Directives issued by the Ministry.

፫/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር የተቀጣሪውን አትሌት የብቃት ማረጋገጫና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች አግባብነት ይመረምራል፣ የቅጥር ውሉን ያጸድቃል፡፡

3/ The relevant federal sports association will examine the appropriateness of the qualification certificate and other detailed information of the employee Athlete, and approve the employment contract.

፬/ የውጭ ሀገር አትሌት በሀገር ውስጥ ስፖርት ክለብ ተቀጥሮ መስራት የሚችለው በዚህ ስራ ህጋዊ ፈቃድ ባለው የንግድ ድርጅት አገናኝነት ነው፡፡

4/ Any foreign Athlete shall be employed in local sport club only through a licensed commercial organization.

፳፱. <u>የአትሌት ማናጀር ወይም ወኪል አስተዳደር</u>

29. <u>Athlete Manager or Agent Management</u>

፩/ ማንኛውም ማናጀር ወይም ወኪል በዚህ ስራ ተገቢውን ህጋዊ ፈቃድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

1/ A manager or an agent shall have the appropriate legal license for this business.

፪/ ሚኒስቴሩ የአትሌት ማናጀር ወይም ወኪል ስለሚሰራበት ሁኔታ የአሰራር መመሪያ ከሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ጋር በመቀናጀት ያወጣል፡፡

2/ The Ministry, in collaboration with the relevant federal sports association, shall issue operational guidelines for the Athlete manager or agent.

፫/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር የአትሌት ማናጀር ወይም ወኪል ከአትሌቱ ጋር የሚያደርገውን የአገልግሎት ውል ያጸድቃል፤

3/ The relevant federal sports association approves the contract of the Athlete's manager or agent with the Athlete.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ያጸደቀውን የአገልግሎት የውል ስምምነት ከእነዝርዝር ማብራሪያው ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ According to Sub-Article (3) of this Article, the relevant federal sports association shall notify to the Ministry with the detailed explanation of the approved service contract.

፭/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የሚወጣውን የመመሪያውን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

፴. የአትሌት ማናጀር ወይም ወኪል ኃላፊነት

ማንኛውም የአትሌቶች ማናጀር ወይም ወኪል የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የአትሌቱን የስልጠና ሂደት በመደገፍ በተገቢው የውድድር ደረጃ እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፪/ አትሌቱን በመወከል የውድድር ተሳትፎና የጥቅማ ጥቅም ውሎችን ይደራደራል፤

፫/ የአትሌቱን የቅጥርና የዝውውር ስርዓት በመከታተል ያስፈጽማል፤

፬/ የአትሌቱን ወቅታዊ ብቃት መሰረት በማድረግ የንግድ ተቋማት መልካም ስሙንና ዝናውን በመጠቀም የንግድ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይደራደራል፤

፭/ የአትሌቱን ደህንነት በስፖርታዊ ዝግጅትና ውድድር ወቅት ይከታተላል፤ ይጠብቃል፤

፮/ በአበረታች ቅመሞች ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ የህግ ጥሰት እንዳይፈጸም ተገቢውን ክትትል ያደርጋል።

፴፩. የአትሌቶች መብትና ግዴታ

፩/ ማንኛውም አትሌት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በስፖርት ስልጠናና ውድድር ያለአድሎ የመሳተፍ፤

5/ The Ministry shall monitor, supervise, and take appropriate action in accordance with the Directive issued pursuant to Sub-Article (2) of this Article.

30. Responsibility of Athlete Manager or Agent

Any Athlete manager or agent shall have the following responsibilities;

1/ Supports the Athlete's training process and facilitates the participation at the appropriate level of competition;

2/ Negotiate the terms of competition participation and benefits on behalf of the Athlete;

3/ Monitors and enforces the Athlete's employment and transfer system;

4/ Negotiate with commercial organization to use Athlete’s good name and reputation to carry out their commercial activities;

5/ Follows and protects the wellbeing of the Athlete during sport preparation and competition;

6/ Creates awareness on anti-doping, prohibits the commission of anti-doping rules violation.

31. Rights and Obligations of Athletes

1/ Any Athletes shall have the following rights.

a) To participate without discrimination in sports training and competition;

ለ) በሚሳተፉባቸው ስፖርታዊ ሁነቶች ላይ ግልፅና ፍትሃዊ መረጃ የማግኘት፤

ሐ) በስፖርት ማህበራት የመሳተፍ፣ የመምረጥና የመመረጥ፤

መ) ስልጠናውን የሚረዱ ግብዓቶች የማግኘትና የመጠቀም፤

ሠ) በሚሳተፉባቸው ስፖርቶች ጥቅም የማግኘት፣ ወይም ሲያሸንፉ እንደአግባብነቱ ሽልማትና ዕውቅና የማግኘት፤

ረ) በስልጠና ወይም በውድድር ወቅት ለሚያጋጥም ጉዳት ሙሉ የህክምና መድህን አገልግሎት የማግኘት፤

ሰ) በስፖርት ተሳትፎ ያገኘውን እውቅና ተጠቅሞ በህጋዊ መንገድ በስሙና ምስሉ ከሚገኘው የኢኮኖሚያዊና የሞራል መብት የማግኘት፤

b) Getting clear and fair information on the sporting events they participate in;

c) Participating in sports associations, voting and being elected;

d) Access to use of training resources;

e) Benefit from the sports in which they participate, or to receive rewards and recognition as appropriate when they win;

f) Access to full medical insurance coverage for injuries sustained during training or competition;

g) To use the recognition gained through participation in sports to legally obtain the economic and moral rights derived from his name and image;

፪/ ማንኛውም አትሌት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በስፖርት ተሳትፎ የሁነቱን ህግና ደንብ ማክበር፤

ለ) የጸረ አበረታች ቅመሞች ህግን ማክበር፤

ሐ) ስፖርታዊ ስነ ምግባሮችን ማክበር፤

መ) ወቅታዊ የጤና ምርመራ የማድረግ፤

ሠ) በአለም አቀፍ ስፖርታዊ ሁነቶች ሀገሪቱን በመወከል በፍጹም ትጋትና በተገቢው ስነ ምግባር የማገልገል፤

ረ) ከስፖርት ሁነት በኋላ ስለውድድሩ ተገቢውን መረጃ የመስጠት፡፡

2/ Athletes have the following obligations:

a) Respecting the rules and Regulations of the sports event;

b) Respecting anti-doping rules;

c) Adherence to sportsmanship;

d) Conducting periodic health check-ups;

e) Representing the country in international sporting events with absolute dedication and proper ethics;

f) Providing relevant information about the competition after the sporting event.

ንዑስ ክፍል ሁለት

የስፖርት ባለሙያዎች አስተዳደር ሥርዓት

፴፪. የስፖርት ባለሙያዎች ምዝገባ

፩/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር ወይም የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋም በዘርፉ የተሰማሩትን የስፖርት ባለሙያዎች ይመዘግባል፣ ለሚኒስቴር ያሳውቃል።

፪/ ሚኒስቴሩ የባለሙያዎችን እና የሙያ ደረጃቸውን በስፖርት የመረጃ ቋት ያደራጃል።

፴፫. የስፖርት ባለሙያዎች ደረጃ አመዳደብ

ማንኛውም የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር በስፖርት ዓይነቱ ተገቢው የስልጠና፣ የትምህርት ደረጃና አግባብነት ያለው የስራ ልምድ መሰረት በማድረግ የስፖርት ባለሙያዎችን ደረጃ ይመድባል፣ አፈፃፀሙም በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፴፬. የውጭ አገር የስፖርት ባለሙያን ስለመቅጠር

፩/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ወይም ክለብ፣ በሀገር ውስጥ በመስኩ ወቅታዊ ውጤት ያስመዘገበ ወይም ብቁ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖሩ ሲረጋገጥ የውጭ ሀገር የስፖርት ባለሙያ ሊቀጥር ይችላል።

፪/ የውጭ ሀገር የስፖርት ባለሙያዎች የክፍያ ስርዓትና የቅጥር መስፈርት ሚኒስቴሩ ከሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ጋር በመተባበር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል።

Sub-Section Two

Sports Professionals Management

32. Registration of Sports Professionals

1/ Any Federal Sport association Sport training Center shall register every sport professional works beneath its administration and Subject to announce the Ministry.

2/ The Ministry shall organize the professionals in levels and register on database.

33. Classification of Sports Professionals

Any federal sports association classifies the level of sports professionals based on the appropriate training, education level and relevant work experience in the type of sport; its implementation is determined by directive to be issued by it.

34. Hiring Foreign Sports Expert

1/ Any federal sports association or club may hire foreign sports expert when it is confirmed that there is no qualified or trained workforce in the country.

2/ The payment system and employment criteria of foreign sports professionals are determined by Directive to be issued by the Ministry in collaboration with the relevant federal sports association.

፫/ የውጭ አገር የስፖርት ባለሙያዎቹ የሀገሪቱን ባለሙያዎች የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት በመለየት ማብቃት ይኖርባቸዋል፡፡

ክፍል አምስት

የስፖርት ሁነቶች አስተዳደርና የሽልማት አሰጣጥ ሥርዓት

ንዑስ ክፍል አንድ

የስፖርት ሁነቶች አመራር ሥርዓት

፴፭. የስፖርት ሁነት ዓይነቶች

፩/ የአገሪቱ ብሔራዊ ቡድን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ስፖርታዊ ሁነቶች ላይ አገሪቱን በመወከል ይሳተፋል፡፡

፪/ ማንኛውም የስፖርት ክለብ የዓለም አቀፍ የክለቦች ሻምፒዮና ሊሳተፍ ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር ወይም የስፖርት ንግድ ተቋም ስፖርታዊ ሁነቶችን በመቅረጽ ሊተገብር ይችላል፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ በሀገር አቀፍ ደረጃ የማህበረሰብ ስፖርት ተሳትፎን የሚያበረታቱ የስፖርታዊ ሁነቶችን በመቅረፅ ሊተገበር ይችላል፡፡

፭/ ሃገር አቀፍ የስፖርታዊ ሁነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታ፤

ለ) ሃገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታ፤

ሐ) ሃገር አቀፍ የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ፕሮግራም ምዘና ውድድር፤

መ) ሃገር አቀፍ ወጣቶች ኦሎምፒክ ጨዋታ፤

ሠ) ሃገር አቀፍ የተማሪዎች ጨዋታ፤

3/ The hired sports expert shall empower the domestic experts by identifying their knowledge and skill gaps.

PART FIVE

Sports Event Management and Award System

Sub-Section One

Sport Event Management System

35. Types of Sports Events

1/ The national team participates in international sporting events representing the country.

2/ Any sports club can participate in the International Club Championship.

3/ Any federal sports association or any sports-related business institution may organize sports events.

4/ The Ministry can implement sports events that promote community sports participation at the national level.

5/ National sporting events are as follows:

a) All Ethiopia game;

b) National Women's Games;

c) National Youth Sports Training Program Evaluation Competitions;

d) National Youth Olympic Games;

e) National Student Games;

ረ) ሃገር አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ስፖርት ፌስቲቫል፤

ሰ) ሃገር አቀፍ የባህል ስፖርት ፌስቲቫል፤

ሸ) ሃገር አቀፍ አርሶ አደርና አርብቶ አደሮች ስፖርት ፌስቲቫል፤

ቀ) ሃገር አቀፍ ሠራተኞች ፌስቲቫል፤

በ) ሃገር አቀፍ የስፖርት ሻምፒዮናዎች፤

ተ) የመከላከያ ወይም የፖሊስ ስፖርት ፌስቲቫል፤

ቸ) ሃገር አቀፍ የክለቦች ሻምፒዮና፤

ነ) የአካል ጉዳተኞች የስፖርት ፌስቲቫል፡፡

፴፮. <u>የስፖርት ሁነቶችን ስለማዘጋጀት</u>

፩/ ማንኛውም ስፖርታዊ ሁነት ህጋዊ ፍቃድ ባለው የስፖርት ንግድ ተቋም ወይም በፌደራል ስፖርት ማህበር ተዘጋጅቶ መተግበር አለበት፤

፪/ በዚህ አዋጅ መሰረት ስፖርታዊ ሁነቶችን የሚያዘጋጅ ማንኛውም የስፖርት ንግድ ተቋም:-

ሀ) በቅድሚያ ከሚመለከተው ፌደራል ስፖርት ማህበር የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርበታል፤

ለ) ለስፖርት ዓይነቱ በፌደራል ስፖርት ማህበራት በወጡ ህጎች መሰረት ሁነቱን አዘጋጅቶ መምራት ይኖርበታል፤

፫/ ማንኛውም ሰው በስፖርት ሁነት ዝግጅት ወቅት የአበረታች ቅመሞች ምርመራ ለማድረግ የሚያስችሉ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት፡፡

f) National Higher Education Institutions Students Sports Festival;

g) National Cultural Sports Festival;

h) National Farmers and pastoralist Sports Festival;

i) National Workers Sports Festival;

j) National Sports Championships;

k) Defense force or Police sport festival;

l) National Club Championships;

m) Persons with Disabilities' Sport Festival.

36. <u>Organizing Sports Events</u>

1/ Any sporting event shall be organized and implemented by a legally licensed sport related business institution or by a federal sports association;

2/ Any sports related institution that organizes sporting events In accordance with this proclamation shall:

a) obtain a technical competency certification from the relevant federal sports association;

b) organize and conduct the event in accordance with the rules established by the relevant federal sports associations ;

3/ Any person shall meet the necessary conditions for Doping test during sporting events.

፬/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር የስፖርት ሁነቶችን የማዘጋጀትና የመምራት ኃላፊነቱን ህጋዊ ፈቃድ ላላቸው ተቋማት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚዘጋጁ የስፖርት ሁነቶች ሚኒስቴሩ ተገቢውን መመሪያ ያወጣል፡፡

4/ The relevant federal sports association may delegate the responsibility of organizing and managing sports events to legally licensed institutions.

5/ The Ministry shall issue the appropriate Directives for sporting events to be organized in accordance with this Proclamation.

፴፯. <u>አለም አቀፍ የስፖርት ሁነቶችን ስለማስተናገድ</u>

፩/ ማንኛውም የስፖርት ንግድ ተቋም በስሙ ያስመዘገበውን ስፖርታዊ ሁነት በሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር በኩል በዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበር ማስመዝገብ ይችላል፤

37. <u>Hosting International Sports Events</u>

1/ Any sports related business institution that brands the sporting event by its own name may, through the relevant federal sports association make the event to be registered at the international sports association;

፪/ ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ሁነትን በአገር ውስጥ ለማስተናገድ የሚፈልግ የስፖርት ንግድ ተቋም ወይም የፌደራል ስፖርት ማህበር በቅድሚያ ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

2/ Any sports related business institution or federal sports association that seeks to host any international sporting event in the country shall first notify the Ministry and obtain permission.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ያገኘ የፌደራል ስፖርት ማህበር የመነሻ ሀሳቡን በማዘጋጀት ለሚመለከተው ዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበር በመላክ ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the federal sports association that obtained the permission shall prepare a proposal and submit it to the relevant international sports association for confirmation.

፴፰. <u>አገር አቀፍ የስፖርት ሁነቶችን ስለማስተናገድ</u>

፩/ ማንኛውም ሃገር አቀፍ የስፖርት ሁነትን የሚያዘጋጅ የስፖርት ንግድ ተቋም ሁነቱን በቅድሚያ በሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ማስመዝገብ አለበት፤

፪/ በዚህ አዋጅ መሰረት ሃገር አቀፍ የስፖርት ሁነት የሚያዘጋጅ የስፖርት ንግድ ተቋም ወይም የፌደራል ስፖርት ማህበር ሁነቱ የሚስተናገድበትን ክልል ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

፫/ ሚኒስቴሩ ሃገር አቀፍ የስፖርት ሁነቶች ስለሚስተናገዱበት አግባብ ተገቢውን የድጋፍና የክትትል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፴፱. <u>በስፖርት ሁነቶች ተሳትፎ ስለማድረግ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገበ ማንኛውም አትሌት ወይም አሰልጣኝ ወይም ክለብ፣ በሃገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ የስፖርት ሁነቶች ላይ ተሳትፎ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም የውጭ ሃገር አትሌት፣ አሰልጣኝ፣ ክለብ፣ ቡድን ወይም የልዑካን ቡድን በሀገር ውስጥ በሚደረጉ የስፖርት ሁነቶች ላይ ለመሳተፍ በቅድሚያ ከላኪው ሃገር እና ከሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ተገቢውን ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

38. <u>Hosting National Sports Events</u>

1/ Any sports related business institution that organizes a national sporting event shall first make the event to be registered by the relevant federal sports association;

2/ Any sports related business institution or federal sports association that organizes a national sporting event In accordance with this Proclamation shall obtain permission from the region to host;

3/ The Ministry conducts appropriate support and monitoring activities regarding the hosting of national sports events.

39. <u>Participation in Sports Events</u>

1/ Any Athlete or coach or club registered in accordance with this proclamation may participate in sports events organized nationally and internationally.

2/ Any foreign Athlete, coach, club, team or delegation to participate in sports events held in the country must first obtain the appropriate permission from the sending country and the relevant international sports association.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ፈቃዱን የሰጠው የፌደራል ስፖርት ማህበር ወደ ሃገር ውስጥ ስለሚገቡት የሁነት ተሳታፊዎች ትክክለኛ መረጃ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3/ According to Sub-Article (2) of this Article, the federal sports association that has granted the permission shall notify the correct information about the participants of the event entering the country to the Ministry.

፵. <u>ለስፖርት ሁነቶች ስለሚደረጉ የውጭ ሀገር ጉዞዎች</u>

40. <u>Foreign Trips for Sports Events</u>

፩/ ማንኛውም በዓለም አቀፍ ስፖርት ሁነት ላይ ለመሳተፍ ወደ ውጭ ሃገር የሚንቀሳቀስ አካል በቅድሚያ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

1/ Any person moving abroad to participate in an international sports event shall first obtain permission from the Ministry.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ለሚንቀሳቀሱ አካላት ሚኒስቴሩ ተገቢውን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

2/ The Ministry provides appropriate support and conducts monitoring and control activities to the entities operating in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

፵፩. <u>የስፖርት ሁነቶችን ስለማገድ</u>

41. <u>Banning Sports Events</u>

በዜጎች ደህንነት፣ ሰላም እና ጤና ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያስከትል ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት ወይም እንደሚከሰት ሲታመን ማንኛውንም የስፖርት ሁነት እንዳይካሄድ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ሪፖርት ሲደርሰው ሚኒስቴሩ ሊያግድ ይችላል፡፡

The Ministry, upon receipt of report from relevant Government body regarding a man-made or natural disaster that has a significant impact on the safety, peace and health of citizens occurs or is believed to occur, may suspend any sporting event.

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

<u>Sub-Section Two</u>

<u>የብሔራዊ ቡድን ዝግጅት</u>

<u>Preparation of The National Team</u>

፵፪. <u>ብሔራዊ ቡድን ስለማቋቋም</u>

42. <u>Establishing a National Team</u>

፩/ የፌደራል የስፖርት ማህበር በተደራጀበት የስፖርት ዓይነት የብሔራዊ ቡድን ማቋቋም አለበት፡፡

1/ Any federal sports association shall establish a national team in the type of sport in which it is organized.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚቋቋመው ብሔራዊ ቡድን ሃገሪቱን የሚወክል ደረጃውን የጠበቀ ስያሜ፣ ትጥቅ፣ አርማና ሰነ ምግባር ሊኖረው ይገባል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

2/ The national team established in accordance with Sub- Article (1) of this Article shall have standard sport apparel and an emblem that represents the country; detail is determined by the Directive to be issued by the Ministry.

፵፫. <u>የብሔራዊ ቡድን ምልመላ</u>

43. <u>Recruitment of the National Team</u>

፩/ ማንኛውም በብሔራዊ ቡድን የሚሳተፍ አትሌት በሃገር ወይም በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ በሚያስመዘግበው ወቅታዊ ውጤት እና ብቃት መሰረት ይመለመላል።

1/ Any Athlete shall be recruited for national team based on his current results and performance of international and national competitions.

፪/ ማንኛውም የስፖርት ክለብ ለብሔራዊ ቡድን የተመረጠን አትሌት በተጠየቀ ጊዜ መላክ አለበት።

2/ Any sports club shall send the selected Athlete to the national team when required.

፫/ የፌደራል ስፖርት ማህበር በብሄራዊ ቡድን አባልነት የሚመለምለውን አትሌት ከአበረታች ቅመሞች ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

3/ Any federal sports association shall recruit doping free Athlete.

፬/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ስለ አትሌት አመራረጥ ተገቢውን መስፈርት ያዘጋጃል፤ ሂደቱንና የተመረጠ አትሌትን በሚመለከት ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል።

4/ The relevant federal sport association shall prepare Athlete selection and recruitment criteria and shall disclose the process of recruitment of Athlete for public.

፭/ በዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ላይ ቅር የተሰኘ አትሌት በዚህ አዋጅ በተቋቋመው የግጭት አፈታት ስርዓት መሰረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

5/ Any Athlete who is dissatisfied with the implementation of this article can lodge complaint according to the dispute resolution system established by this Proclamation.

፵፬. የብሄራዊ ቡድን አሰልጣኞች ምደባ

፩/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ተገቢውን መስፈርት በማስቀመጥ ባስመዘገቡት ውጤት የብሔራዊ ቡድን አሰልጣኞችን ይመድባል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀሙ ላይ ቅር የተሰኘ አሰልጣኝ በዚህ አዋጅ በተቋቋመው የግጭት አፈታት ስርዓት መሰረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፵፭. የብሔራዊ ቡድን ዝግጅት

፩/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ብሔራዊ ቡድኑን በዝግጅትና ውድድር ወቅት የሚመራና የሚያስተባብር አካል ይመድባል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ለተመረጡ ብሔራዊ ስፖርታዊ ውድድሮች የበጀት ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፤ የውድድሩን ሂደት ይከታተላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

፫/ ሚኒስቴሩ የብሔራዊ ቡድኑን ዝግጅትና የውድድር ሂደቱን የሚከታተል፣ የሚደግፍና የሚቆጣጠር አካል ያደራጃል፡፡

፵፮. የብሔራዊ ቡድን የተሳትፎ ሥነ ሥርዓት

፩/ ሚኒስቴሩ ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ጋር በመቀናጀት ለተሳትፎ የሚንቀሳቀሰውን ብሔራዊ ቡድን ቃለ መሐላ በማስገባት የሽኝት መርሃ ግብር ይፈጽማል፤ አጠናቆ ሲመለስ ተገቢውን አቀባበል ያደርጋል፡፡

44. Assigning of National Team Coaches

1/ The relevant federal sports association assigns national team coaches based on the results achieved by setting criteria, the details are determined by Directive.

2/ Any coach who is dissatisfied with the implementation of this Article, Sub-Article (1) may lodge complaint in accordance with the dispute resolution system established by this Proclamation.

45. Preparation of the National Team

1/ The relevant federal sports association assigns a body to manage and coordinate the national team during preparation and competition.

2/ The Ministry may support selected national sport competitions in budget, monitors and supports the competition process; detail is determined by Directive.

3/ The Ministry shall organize the Supervisory and regulatory body to support the national team preparation and competition process.

46. Participation Procedure of the National Team

1/ The Ministry, in coordination with the relevant Governmental body, shall administer the oath of the national team for participation and carry out the accompany program; it gives proper reception when return.

፪/ ብሔራዊ ቡድኑ ዓለም አቀፍ ውድድሮች በመሳተፍ ሃገሪቱን በተገቢው ክብርና ሙያዊ ስነ ምግባር ይወክላል፡፡

፫/ በብሔራዊ ቡድን የሚሳተፍ አትሌት ወይም የስፖርት ባለሙያ በውድድር ወቅትና በብሔራዊ ቡድን ቆይታዎች ከማንኛውም የሃገርን ገፅታ ከሚያጎድፉ ተግባራት መቆጠብ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ አትሌት ወይም የስፖርት ባለሙያ ከማንኛውም ቀጣይ የብሔራዊ ቡድን ተሳትፎ ይሰናበታል፡፡

2/ The national team represents the country by honor and professional ethics in international competitions.

3/ Any Athlete or sports professional who participate in the national team shall refrain from any activities that damage the image of the country during the competition and at any representations.

4/ Any Athlete or sports professional who infringes Sub-Article (3) of this Article is fired from any further participation in the national team and related benefits.

ንዑስ ክፍል ሦስት
የስፖርት ሽልማት አሰጣጥ ሥርዓት

Sub-Section Three
Sports Award System

፵፯. የስፖርት ሽልማት አሰጣጥ

47. Grant of Sports Awards

፩/ ሃገሪቱን በመወከል በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤት ላስመዘገቡ አትሌቶች፣ የስፖርት ባለሙያዎችና የብሔራዊ ቡድን አባላት እንደ ውድድሩ ደረጃና እንደተሳትፎው መጠን ሽልማትና እውቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡

1/ Awards and recognition may be given for Athletes, sports professionals and national team members who have achieved results in international competitions by representing the country depending on the level of the competition and the amount of participation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ የሃገሪቱን የስፖርት እድገት በዕውቀት፣ በችሎታ እና በሀብት በመደገፍ የላቀ አስተዋጽዎ ላበረከቱ ወይም ረጅም ዘመን ላገለገሉ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ሽልማት ይሰጣል፡፡

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, an award is given by the Ministry for those individuals or institutions that have made outstanding contributions or have served for a long time by supporting the country's sports development with knowledge, skills and resources.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሠረት የሚሰጠው ሽልማት እንደ አግባብነቱ በዓይነትና በገንዘብ ወይም ልዩ ሃገራዊ ሽልማት እና የምስክር ወረቀት ሊሆን ይችላል፤ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

ክፍል ስድስት

ስለስፖርት ፋይናንስ አስተዳደር

ንዑስ ክፍል አንድ

የስፖርት ኢንቨስትመንት

፵፰. ስለስፖርት ኢንቨስትመንት

በህግ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት ተቋም የስፖርት ኢንቨስትመንት ስለሚበረታታበት አግባብ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል።

፵፱. የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ማረጋገጫ

፩/ ሚኒስቴሩ በሃገር ውስጥ የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ለሚያመርቱ እና ከውጭ ሃገር ለሚያስገቡ ተቋማት ተገቢውን መስፈርት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማዘጋጀት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል።

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት ለሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ተገቢውን የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል።

3/ The award given in accordance with Sub-Article (1) and (2) of this Article may be in kind, money or special national title and certificate as appropriate; the details shall be determined by Regulation to be issued by Council of Ministers.

PART SIX

Sports Finance Management

Sub-Section One

Sport Investment

48. Sports Investment

The relevant Government organ shall establish appropriate work procedures to Incentivize sports investment.

49. verifying of Sports Equipment and Sport Apparel

1/ The Ministry, in collaboration with relevant Government body, establishes appropriate standards and issues certificates of qualification for organizations that produce and import sports equipment and Apparel in the country.

2/ The Ministry shall develop the appropriate procedure for the certification of qualification provided in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

፶. <u>የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ማበረታቻ ሥርዓት</u>

፩/ ሚኒስቴሩ በሃገር ውስጥ የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ለሚያመርቱ አካላት ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በመተባበር የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ከውጭ ሃገር በድጋፍ ወይም ከቀረጥ ነፃ በሚገቡ የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

፶፩. <u>የስፖርት ንግድ</u>

፩/ ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ነክ ንግድ እንዲስፋፋ ተገቢውን አሰራር ይዘረጋል፡፡

50. <u>Sports Equipment and Sport Apparel Incentive System</u>

1/ The Ministry, in collaboration with relevant Government body, establishes appropriate standards and issues certificates of qualification for organizations that produce sports equipment and sport apparel in the country.

2/ The Ministry shall conduct proper monitoring and control of sports equipment and sport apparel imported from foreign countries by incentive.

51. <u>Sports Related Business</u>

The Ministry, in collaboration with the relevant parties, develops appropriate procedures for the expansion of sports-related business.

<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>
<u>የፌደራል ስፖርት ማህበራት የፋይናንስ አስተዳደር</u>

<u>Sub-Section Two</u>
<u>Financial Management of Federal Sports Associations</u>

፶፪. <u>የፌደራል የስፖርት ማህበር የገቢ ምንጭ</u>

፩/ ማንኛውም የፌደራል የስፖርት ማህበር ከሚከተሉት ምንጮች ገቢ ሊሰበስብ ይችላል፡-

ሀ) ከአለም አቀፍ ስፖርት ማህበራት የሚሰጣቸው የፋይናንስ ድጋፎች፤

ለ) ከውድድር ትኬት እና ከስፖርታዊ ሁነቶች ሽያጭ፤

ሐ) ከስፖርት ክለቦች የሚሰበሰብ መዋጮ፤

መ) ከአትሌት ዝውውር የሚገኝ፤

52. <u>Source of Income of Federal Sports Association</u>

1/ Any federal sports association may collect income from the following sources:

a) Financial support from the International Sports Association;

b) From the sale of tournament tickets and sporting events;

c) Contributions collected from member sport club;

d) Revenue from Athlete transfers;

ሠ) ከሚዲያ ሽፋንና ከማስታወቂያ ስራ የሚገኝ፤

ረ) ከሚሰጡት አገልግሎት የሚሰበሰብ፤

ሰ) ከተለያዩ ስፖርት ነክ ንግዶች የሚገኝ፤

ሸ) ከስፖንሰርሺፕ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ሃገራቱ ውጤት በማስመዝገብ የምትታወቅባቸውን ስፖርቶችና ሀገራዊ እምቅ የስፖርት ሀብትን በመለየት እንዳግባብነቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፤ አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል።

፶፫. <u>የፌደራል ስፖርት ማህበራት የፋይናንስ አጠቃቀም ሥርዓት</u>

፩/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት የሚያገኟቸውን ገቢዎች ተገቢውን የፋይናንስ ስርዓት በመከተል ለታለመለት ዓላማ ብቻ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

፪/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት ሀገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች የሂሳብ ቁጥር ከፍተው ያንቀሳቅሳሉ።

፫/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን በየወቅቱ ተከታትለው በሚመለከተው ህጋዊ አካል ማስመርመር አለባቸው።

፬/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት የሒሳብ ምርመራ ሪፖርቱን ለሚኒስቴሩ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

e) Income from media coverage and advertising;

f) Revenue collected from services provided;

g) Income from various sports-related businesses;

h) Income from sponsorships.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Government may provide support for identified national sport potential resources and sports in which the country is known for achieving results; the implementation is determined by Directive.

53. <u>Financial use of Federal Sports Associations</u>

1/ Federal sports associations shall use the income only for the intended purpose with appropriate financial system.

2/ Federal sports associations open and operate bank accounts in the country.

3/ Federal sports associations shall monitor their financial use every season and be audited by the relevant legal entity.

4/ Federal sports associations shall regularly report the audit report to the Ministry at the end of every fiscal year.

፫/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ከመንግስት የሚሰጣቸውን የፋይናንስ ድጋፍ በመንግስት የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ህጎች መሰረት መጠቀም አለባቸው፡፡

5/ Any federal sports association, which obtains financial support in accordance with Sub-Article (2) of Article 52 of this Proclamation, shall use the finance in accordance with the Government's procurement and financial management laws.

፶፬. የፋይናንስ አጠቃቀም ክትትልና ድጋፍ

54. Monitoring and Support of Financial Use

፩/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት፣ ገቢያቸውን ስለሚሰበሰቡበትና ስለሚጠቀሙበት አግባብ መመሪያ በማዘጋጀት በጠቅላላ ጉባኤ ማጸደቅ አለባቸው፡፡

1/ Federal sports associations shall prepare income collection and use Directive and submit it for general assembly for approval.

፪/ ሚኒስቴሩ የፌደራል ስፖርት ማህበራት ያገኟቸውን ገቢዎች አጠቃቀም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

2/ The Ministry monitors, supervises and take appropriate action on the use of the income earned by the Federal sports associations.

፶፭. የክትትልና ቁጥጥር ኃላፊነት

55. Duty of Supervision and Control

፩/ ማንኛውም የፌደራል የስፖርት ማህበር፡-

1/ Any federal sports association shall have the following duties:

ሀ) የስፖርት ክለቦች ለአሰልጣኞችና ለአትሌቶች የሚከፍሉት ክፍያ ግልፅና ተመጣጣኝ ዋጋ መፈጸሙን መቆጣጠርና መከታተል አለባቸው፡፡

a) Monitors the fairness and transparency of sport club payments to coaches and Athletes.

ለ) ክለቦች ዘላቂ ሕልውናቸውን አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ ከገቢያቸው በላይ ወጪ እንዳያወጡ መከታተል አለባቸው፡፡

b) Supervises sport clubs not to spend more than their income in a manner that jeopardizes their sustainable existence.

ሐ) ክለቦች በየዓመቱ ሂሳባቸውን በውጪ ኦዲተር ማስመርመራቸውን መቆጣጠር አለባቸው፡፡

c) Monitors' sport clubs properly manage their accounts audited annually by an external auditor.

፪/ ማንኛውም ክለብ ሃገር አቀፍ ስፖርት ማህበሩ የሚያወጣውን ህግና መመሪያን አክብሮ መንቀሳቀስ አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር በዚህ አንቀጽ የተገለጹትን ግዴታዎች ተላልፎ በተገኘ የስፖርት ክለብ ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

ንዑስ ክፍል ሶስት
የፌደራል ስፖርት ልማት ፈንድ

፶፮. መቋቋም

፩/ የፌደራል ስፖርት ልማት ፈንድ ከዚህ በኃላ "ፈንድ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ስለፈንዱ የገቢ ምንጭ፣ ስለገቢ አሰባሰብና አከፋፈል፣ ስለ ድጋፍ መስክ እና ስለፈንዱ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

ክፍል ሰባት
የስፖርት ግጭት አፈታት ሥርዓት

፶፯. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም

፩/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር በተሰማራበት የስፖርት ዓይነት የሚነሱ አቤቱታዎችና ቅሬታዎችን የሚፈታ ኮሚቴ ማዋቀር አለበት፡፡

፪/ የኮሚቴው አባላትና አወቃቀር በፌደራል ስፖርት ማህበር እንደ አግባብነቱ ይወሰናል፡፡

2/ Any sport club must act in accordance with the Rules and Regulations issued by the federal sports association.

3/ Any federal sports association should take appropriate administrative action against a sports club found to have violated the obligations described in this article.

Sub-Section Three
Federal Sports Development Fund

56. Establishment

1/ The federal Sports Development Fund hereinafter referred to as the "**Fund**" is hereby established in this Proclamation.

2/ Regarding source of income, collection and distribution, field of support and management of the fund is determined by Regulation to be issued by Council of Ministers.

PART SEVEN
Sports Dispute Resolution System

57. Establishment of Grievance Handling Committee

1/ Any federal sports association shall set up committee to resolve grievances arising from the type of sport it is engaged in.

2/ The members and structure of the committee is determined by the Federal Sports Association as appropriate.

፫/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር የኮሚቴው አባላት የስራ ዘመን እና ስለሚመራበት ሁኔታ የአሰራር ሥርዓት ይወስናል።

3/ The relevant federal sports association shall determine the committee's term of office and the procedure for its management.

፶፰. በኮሚቴው ስለሚታዩ ጉዳዮች

58. Issues to be Considered by the Committee

፩/ ኮሚቴው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡-

1/ The committee shall, receiving grievances submitted to it, render decisions on the following issues:

ሀ) የፌደራል ስፖርት ማህበራት የአመራሮች ምርጫ አፈጻጸም፤

a) Execution of federal sport associations' election of leaders;

ለ) የፌደራል ስፖርት ማህበራት የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም፤

b) Collection and use of resources of federal sport associations;

ሐ) የአትሌቶችና የስፖርት ባለሙያዎች ምልመላና መረጣ፤

c) Recruitment and selection of Athletes and sports professionals;

መ) የአትሌቶችና የስፖርት ባለሙያዎች ቅጥርና ዝውውር አግባብነት፤

d) The relevant of employment and transfer of Athletes and sports professionals;

ሠ) የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ፤

e) Provision of referee services;

ረ) ትንኮሳና አድሏዊነት፤

f) Harassment and discrimination;

፪/ ኮሚቴው በማህበሩ በሚደረጉ ስፖርታዊ ሁነቶች ላይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤትን በማቋቋም በወቅቱ የሚነሱና አስቸኳይ ውሳኔ የሚሹ ቅሬታና አቤቱታዎችን በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል።

2/ The committee establishes temporary office for sports events held by the association and investigate and solve complaints that arise at the time and require an urgent decision.

፫/ ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የቀረቡለትን አቤቱታዎች ከቀረበለት ቀን አንስቶ ባለት በ፲ (ዐሥር) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

3/ The committee shall make a decision on the petitions submitted to it under Sub-Article (1) of this Article with in 10 (Ten) consecutive days from the date of submission.

፬/ በኮሚቴው ስልጣን ስር የማይወድቁ ስፖርታዊ አለመግባባቶችን እንዲሁም ኮሚቴው አይቷቸው ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማይባልባቸውን ጉዳዮች ተቀብሎ ውሳኔ የሚሰጥ የስፖርት ግልግል ጉባኤ ይቋቋማል። ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

፶፱. <u>ይግባኝ ስለማቅረብ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ)፣ (መ) እና (ረ) ላይ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ውሳኔ ከተሰጠው ቀን አንስቶ ባሉት ፴ (ሰላሳ) የስራ ቀናት ይግባኝ አቤቱታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔ ከተሰጠው ቀን አንስቶ ባሉት ፷ (ስልሳ) ቀናት ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውም ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

<u>ክፍል ስምንት</u>
<u>መረጃ ሥርዓት</u>

፷. <u>የስፖርት መረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ሥርዓት</u>

፩/ ሃገራዊ የስፖርት ሀብቶች በአግባቡ ተመዝግበው በመረጃ ቋት መያዝ አለባቸው።

4/ Sport Tribunal Council is established to see cases that don't fall under the jurisdiction of the committee and decisions of Committee for which an appeal is not lodged for a Regular Court. The details shall be determined by Regulations to be issued by the Council of Ministers.

59. <u>Lodging of Appeal</u>

1/ A party dissatisfied by the decision given on Sub-Article (1), (b), (d) and (f) of Article 58 of this Proclamation may lodge his appeal to the Federal High Court within 30 (Thirty) working days from the date of the decision.

2/ Any party who dissatisfied by the decision given in accordance with Sub-Article (1) of this Article may appeal to the Federal Supreme Court within 60 (Sixty) days up on receiving the decision; the decision of the Supreme Court shall be final.

<u>PART EIGHT</u>
<u>Information System</u>

60. <u>Sports Information Management</u>

1/ National sports resources should be properly recorded and maintained in a database.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሰረት የሚደራጀው የመረጃ ቋት በሃገሪቱ እንቅስቃሴ የሚደረግባቸው የስፖርት ዓይነቶች፣ አትሌቶች፣ የስፖርት ባለሙያዎች፣ ክለቦች፣ የስፖርት ማህበራት፣ የማሰልጠኛ ተቋማትን፣ የስፖርት ማዘውተሪያዎችንና የሀገራችን የተሳትፎ ታሪካዊ መረጃዎችና ውጤቶችን መያዝ አለበት።

2/ The database organized according to Sub-Article (1) of this Article must contain the types of sports that are practiced in the country, Athletes, sports professionals, clubs, sports associations, training institutions, sports events and historical data and competition results of our country's participation.

፫/ ሚኒስቴሩ የሃገሪቱን የስፖርት የመረጃ ቋት በዘመናዊ መልክ ያደራጃል፣ በየጊዜው መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል፣ ለማህበረሰቡ በተለያዩ ዘመናዊ ዘዴዎች ተደራሽ ያደርጋል።

3/ The Ministry organizes the national sports database in a modern way; updates the information regularly and makes it accessible to the community through various modern methods.

፬/ ሚኒስቴሩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የሃገሪቱን ታሪካዊ የስፖርት ሀብቶችን በማሰባሰብ በአውደ ርዕይ ለህዝብ ተደራሽ የሚያደርግ የስፖርት ቤተ መዘክር ሊያቋቁም ይችላል።

4/ The Ministry may establish a sports museum in cooperation with the relevant body to collect the country's historical sports resources and make them accessible to the public through exhibitions.

፷፩. <u>መረጃ የመያዝ ኃላፊነት</u>

61. <u>Liability to Hold Information</u>

፩/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር ስለሚያስተዳድረው ፕሮጀክትና ፕሮግራም ዝርዝር መረጃ መያዝ አለበት።

1/ Any federal sports association must have detailed information about the project and program it manages.

፪/ የፌደራል ስፖርት ማህበር የያዘውን መረጃ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ አለበት።

2/ The Federal Sports Association must make the information available to the public using modern technology.

፷፪. <u>የመረጃ ስርጭትና አጠቃቀም ሥርዓት</u>

62. <u>Distribution and use of Information</u>

፩/ የፌደራል ስፖርት ማህበር የብሔራዊ ቡድን አትሌትና አሰልጣኝ ምርጫና ዝግጅትን በተመለከተ ግልፅ መረጃ ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

1/ The Federal Sports Association shall provide clear information to the public regarding the selection and preparation of the national team's Athlete and coach.

፪/ ማንኛውም የስፖርት ተቋማት ግልጽና ትክክለኛ መረጃ ለመገናኛ ብዙሃን መስጠት አለበት፡፡

፫/ የመገናኛ ብዙሃን የስፖርት ሁነት ዝግጅትና አፈጻጸም እንዲሁም ሃገራዊ የስፖርት ልማት ላይ ግልጽና ትክክለኛ መረጃ ለህብረሰተሰቡ ማድረስ አለባቸው፡፡

ክፍል ዘጠኝ

የተከለከሉ ተግባራት እና ቅጣት

፷፫. በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የተከለከሉ ተግባራት

በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚከተሉትን መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

፩/ በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ውስጥ ማናቸውንም ዓይነት በቃል፣ በዜማ፣ በጽሁፍ፣ በምልክት እና በአለባበስ የሚገለፁ መልካም ሥነ ምግባርን የሚፃረሩና ሁከትን ሊያነሳሱ የሚችሉ ድርጊቶች መፈፀም የተከለከለ ነው፤

፪/ የዘረኝነት እና የማህበራዊ ልዩነትን የሚያንፀባርቁ ማናቸውንም ዓይነት ድርጊቶች መፈፀም፤

፫/ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ከመጀመራቸው በፊት ወይም በሚካሄዱበት ወቅት ማንኛውንም አይነት የፖለቲካ ወይም ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን ማካሄድ፤

፬/ በሰው ጤና፣ አካል ወይም ስነ ልቦና ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ስለታማ መሳሪያዎችን፣ የተለያዩ የሚተኮሱ፣ የሚወረወሩ፣ የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ ወይም መርዛማ ቁሳቁሶችን ይዞ መግባት፤

2/ Any sports institutions must provide clear and accurate information to the media.

3/ The mass media must deliver clear and accurate information to the public on the preparation and performance of sports events and national sports development.

PART NINE

Prohibitions and Penalty

63. Prohibited Activities in Sports Facilities

The following activities are prohibited in sports facilities:

1/ Committing an act that causes damage on the sports facilities or Committing any kind of verbal or musical or written or symbolic or dress-related actions that violate good morals and may incite violence in and around the sports venue;

2/ Committing any kind of actions that reflect racism and social discrimination;

3/ Conducting any kind of political and religious agitations before and during sports activities and after the completion;

4/ Bringing inside sharp weapons or various shooting or throwing or exploding or inflammable or toxic materials that causes harm to human health or body or psychology;

፷፬. ስለአበረታች ቅመሞች

፩/ ማንኛውም አትሌት በስፖርት አካላዊና ስነ ልቦናዊ የበላይነትን ለማግኘት በማሰብ አበረታች ቅመሞችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ለአትሌት አበረታች ቅመሞችን እንዲጠቀም ማዘዝ ወይም መስጠት ወይም መጠየቅ ወይም ማመቻቸት ወይም ማስገደድ የተከለከለ ነው፡፡

፫/ ማንኛውም ሰው ለፀረ አበረታች ቅመሞች መከላከል ለሚደረግ የቁጥጥርና የምርመራ ተግባር የመተባበር ግዴታ አለበት።

፬/ አበረታች ቅመሞችን ያለፈቃድ ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት፣ ማምረት፣ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ ማዘዋወር ወይም ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው።

፷፭. ስፖርታዊ ማጭበርበር

፩/ ለፌደራል ስፖርት ማህበር አመራር ወይም አባል ሆኖ ለመመረጥ በማሰብ፣ ለተለያዩ አካላት የገንዘብ ወይም የተለያዩ ስጦታዎችን በመስጠት ማባበል የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የማንኛውም የስፖርት ውድድሮች ወይም ሁነት ውጤትን ለማስቀየር ለአትሌት፣ ለዳኛ፣ ለአሰልጣኝ፣ ለቡድን መሪ ወይም ለሌሎች ሰዎች ገንዘብ መስጠት፣ መቀበል፣ ማስገደድ፣ ድርድር ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

64. About doping

1/ Any Athlete, with intent to gain physical and psychological superiority in sport, is prohibited from using doping.

2/ Any person is prohibited to prescribe or give or ask or induce or force Athletes to use doping.

3/ Any person shall cooperate during the control and testing of doping.

4/ Importing, producing, selling, distributing, trafficking or possessing any doping without permission is prohibited.

65. Sporting Fraud

1/ Inducing by giving money or various gifts to various parties to be elected as a leader or member of a federal sports association is forbidden.

2/ Giving or accepting money from; or coercing or negotiating with an Athlete or judge or coach or team leader or relevant body to change the result of any sports competition or event with the intent to obtain for him or for other unlawful enrichment is forbidden.

፷፮. <u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

፩/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ህጎች የተደነገጉ ጥፋቶችን በፈፀመ አካል ላይበዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

፪/ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ሰው ቀላል የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፩) በመተላለፍ የስራ አፈፃፀምና የፋይናንስ አጠቃቀምን አስመልክቶ በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያላቀረበ፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፫) በመተላለፍ ሚኒስቴሩ ለሚያከናውነው ክትትልና ቁጥጥር ተገቢውን መረጃ በመስጠት ያልተባበረ፤

ሐ/ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው መመሪያ መሰረት ዓመታዊ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ያላካሄደ፤

መ/ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣው መመሪያ የተደነገገውን የፌደራል ስፖርት ማህበራት የስብሰባ ስነ ስርዓት ያላከበረ፤

66. <u>Administrative Measures</u>

1/ The Ministry shall take the administrative measures listed under this Article against any person that commits an act prohibited under this Proclamation or any laws issued for the implementation thereof.

2/ A simple written warning shall be issued to any person who commits any of the following wrongful acts:

a) Failure to submit quarterly reports to the Ministry regarding work performance and financial utilization in contrary with Sub-Article (1) of Article 14 of this Proclamation;

b) Failure to cooperate by providing appropriate information for the monitoring and supervision activities conducted by the Ministry contrary to Sub-Article (3) of Article 14 of this Proclamation;

c) Failure to conduct an annual general assembly meeting in accordance with the Directives to be issued following this Proclamation;

d) Failure to observe the meeting procedures of federal sports associations as prescribed in the Directives to be issued under this Proclamation;

ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፩ ንዑስ አንቀፅ (፩) በመተላለፍ የፌደራል ስፖርት ማህበር ስለሚያስተዳድረው ፕሮጀክትና ፕሮግራም ዝርዝር መረጃ ያልያዘ፤

፫/ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ሰው ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ በመተላለፍ የማዘውተሪያ ስፍራ ፈቃድ ሳይኖረው የማዘውተሪያ ስፍራ የገነባ፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ በመተላለፍ የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው የማዘውተሪያ ስፍራን ለአገልግሎት ያዋለ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ በመተላለፍ የማዘውተሪያ ስፍራን በህግ ላልተፈቀደ አገልግሎት ያዋለ፤

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀፅ (፬) በመተላለፍ ያጸደቀውን የውጭ ሃገር አትሌት የአገልግሎት የውል ስምምነት ከእነዝርዝር ማብራሪያው ለሚንስቴሩ ያላሳወቀ፤

ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀፅ (፫) በመተላለፍ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡት የሁነት ተሳታፊ የውጭ ሀገር ዜጎች ትክክለኛ መረጃ ለሚኒስቴሩ ያላሳወቀ፤

e) Failure to maintain detailed information regarding projects and programs administered by a federal sports association in contrary to Sub-Article (1) of Article 61 of this Proclamation;

3/ A rigorous written warning shall be issued to any person who commits any of the following acts:

a) Construction of a sports facility without obtaining a permit in contrary to Article 20 of this Proclamation;

b) Offering a sport facility for service without a certificate of competence in contrary to Article 22 of this Proclamation;

c) Utilizing a sports facility for unlawful purpose in contrary with Article 23 of this Proclamation;

d) Failure to notify the Ministry of the approved terms of employment contracts for foreign Athletes and detailed explanations in contrary to Sub-Article (4) of Article 29 of this Proclamation;

e) Failure to provide the Ministry with accurate information about foreign citizens entering the country for event participation in contrary to Sub-Article (3) of Article 39 of this Proclamation;

ረ/ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሰረት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የፈቃድ እድሳት ሳይኖረው በየትኛውም የስፖርት ማህበር ስም የተንቀሳቀሰ ወይም ስፖርታዊ ሁነት ላይ የተሳተፈ ወይም ያዘጋጀ፤

ሰ/ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሰረት በፌደራል ስፖርት ማህበር ቦርድ አባልነት ወይም በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት መሥራት የማይችል ሰው አካቶ ከተገኘ፤

ሸ/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀፅ (፫) በመተላለፍ የፌደራል ስፖርት ማህበር ገቢውን በሕጋዊ አካል ያላስመረመረ እንደሆነ፤

ቀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ስር የተጠቀሰ ቀላል የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጥ ጥፋትን በተደጋጋሚ ጊዜ ከፈፀመ፡፡

፬/ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ሰው በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተገነገውን በመተላለፍ ተገቢውን ክትትል ባለማድረግ አትሌቱ ለአበረታች ቅመሞች የህግ ጥሰት የተጋለጠ እንደሆነ ከ፻ሺህ እስከ ፪፻ሺህ (ከመቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

f) Operating under the name of any sports association without a valid registration certificate or license renewal in accordance with the Directive to be issued under this Proclamation;

g) Inclusion of an individual as a board member or executive committee member of a federal sports association who is ineligible to serve under the Directive to be issued pursuant to this Proclamation;

h) Any federal sports association that fails to have its income audited by a legal auditor in accordance with Sub-Article (3) of Article 53 of this Proclamation;

i) Committing a wrongful act that warrants a simple written warning under Sub-Article (2) of this Article repeatedly.

4/ Any person who commits any of the following acts shall be punished with a fine:

a) Any person, who, in violation of Sub-Article (6) of Article 30 of this Proclamation, fails to perform appropriate supervision, thereby exposing an Athlete to a doping violation, shall be punished with a fine ranging from 100,000 ETB to 200,000 ETB (One-Hundred Thousand to Two-Hundred Thousand);

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፩) በመተላለፍ ህጋዊ አሰራርን ያልተከተለ ወይም በህጋዊ አሰራር ሽፋን አላማውን የሳተ የውጪ ግንኙነት ወይም ጉዞ የፈጸመ ፻ሺህ ብር (አንድ መቶ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

b) Any person who violates the procedures set out in Sub-Article (1) of Article 40, fails to follow legal procedures, or conducts foreign relations or travel that deviates from its objective under the guise of legal procedures shall be punished with a fine of 100,000 ETB (One-Hundred Thousand);

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) በመተላለፍ ለብሔራዊ ቡድን የተመረጠን አትሌት በወቅቱ ያልላከ የስፖርት ክለብ ፷፭ ሺህ ብር (ሰባ አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

c) Failure to send an Athlete by sport club selected for the national team in a timely manner in contrary to Sub-Article (2) of Article 43 of this Proclamation shall be punished with fine of 75,000 ETB (Seventy Five Thousand);

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) በመተላለፍ የሃገርን ስም ወይም ገፅታ የሚያጠፋ ተግባራት የፈፀመ አትሌት ወይም የስፖርት ባለሙያ በቅድሚያ ፷፭ ሺህ ብር (ሰባ አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

d) Any Athlete or sports professional who commits an act jeopardizing the name or image of the country in contrary with Sub-Article (3) of Article 46 of this Proclamation, shall first be punished with a fine of 75,000 ETB (Seventy Five Thousand);

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀፅ (፩) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ የፌደራል ስፖርት ማህበር ያገኘውን ገቢ ከታለመለት ዓላማ ውጪ የተጠቀመ እንደሆነ፤ እንደነገሩ አግባብነት ከ፴ሺህ (ሰላሳ ሺህ) እስከ ፻ሺህብር (መቶ ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

e) Utilization of income collected by a federal sports association for purposes other than its intended objectives in contrary with Sub-Article (1) of Article 53 of this Proclamation shall be punished with a fine of 30,000 ETB (Thirty Thousand) up to 100,000 ETB (One Hundred Thousand).

፭/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሰረት በሚሰጠው ማስጠንቀቂያ የተፈፀመውን ጥፋት፣ ጥፋቱ የሚታረምበትን ጊዜና አግባብ እንዲሁም ከጥፋቱ ካልታረመ በቀጣይ የሚወሰድበትን እርምጃ በግልጽ በመጥቀስ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

፮/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ስር የተጠቀሱትን ጥፋቶች ከሁለት ጊዜ በላይ የፈፀመን ሰው እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ ሊያግድ ይችላል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሰረት የሚወሰድ የእግድ እርምጃ የተፈፀመውን የሕግ ጥሰት፣ እግዱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ እና ሊደረግ የሚገባውን ማስተካከያ በግልጽ በሚያሳይ ሁኔታ በፅሁፍ መሰጠት አለበት።

፰/ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ጥፋቶችን የፈፀመ ሰው እንዲሰረዝ ይደረጋል፡-

ሀ) ከሶስት ጊዜ በላይ ተደጋጋሚ የእግድ እርምጃ የተወሰደበት ሲሆን፣

ለ) የሃገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በሚጎዳና በወንጀል በሚያስጠይቅ አደገኛ ተግባራት ላይ የተሰማራ እንደሆነ፣

ሐ) ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚያሰርዝ ድርጊት ላይ የተሰማራ እንደሆነ፣

5/ The warning issued by the Ministry under Sub-Articles (2) and (3) of this Article shall be in writing and shall clearly state the wrongful acts committed, the period and manner in which the act shall be rectified, and the subsequent measures to be taken if the wrongful act is not corrected.

6/ The Ministry may suspend any person, for Six month, who has committed the acts listed under Sub-Article (4) of this Article for more than two times.

7/ Any suspension measure taken under Sub-Article (6) of this Article shall be provided in writing and shall clearly show the wrongful act committed, the duration of the suspension, and the necessary rectifications to be made.

8/ The person who commits one or more of the following wrongful acts shall be cancelled:

a) Where a suspension measure has been taken against the person for more than three times;

b) Engaging in dangerous activities that harm the national interest of the country and entail criminal liability;

c) Engaging in acts that cause cancellation as prescribed under the Regulation and Directives to be issued following this Proclamation;

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) መሰረት የሚወሰድ የመሰረዝ እርምጃ የተፈፀመውን ጥፋት፣ እርምጃውን ለመውሰድ መነሻ የተደረገ የሕግ መሰረት እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በግልጽ በሚያሳይ ሁኔታ በፅሁፍ መሰጠት አለበት።

9/ A cancellation measure taken under Sub-Article (8) of this Article shall be provided in writing and shall clearly show the wrongful acts committed the legal basis for the measure, and other relevant details.

፷፯. <u>ቅጣት</u>

ማንኛውም ሰው፡-

67. <u>Penalty</u>

Any person:

፩/ በአንቀጽ ፷፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ አግባብበነት ባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሰረት ይቀጣል፡፡

1/ Commits the prohibited activities stipulated in Sub-Article (1) and (2) of Article 63 of this Proclamation shall be punished with appropriate penal law provisions;

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፫ በንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ሰው እንደነገሩ አግባብነት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2/ Violates of the activities stipulated in Sub-Articles (3) of Article 63 of this Proclamation shall be punished by simple imprisonment of up to three years and a fine of up to Fifty Thousand Birr.

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፫ ንዑስ አንቀፅ (፬) የተደነገውን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ ማንኛውም ሰው እንደነገሩ ሁኔታ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

3/ Violates the provisions of Sub-Article (4) of Article 63 of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment up to Five years.

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፬ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም አትሌት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከአንድ መቶ ሺህ ብር እስከ ሦስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4/ An Athlete found to be violating Sub-Article (1) of Article 64 of this Proclamation shall be punished up to Five years simple imprisonment or a fine of between One Hundred Thousand Birr up to Three Hundred Thousand Birr.

፭/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፬ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው እንደነገሩ ሁኔታ እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፮/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፬ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው ሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፯/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፰/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው እስከ ዐሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፱/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፷፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከዐሥር ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

ክፍል ዐሥር
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፷፰. ደንብና መመሪያ ስለማውጣት

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

5/ Found violating in Sub-Article (2) of Article 64 of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding Seven years and a fine up to Five Hundred Thousand Birr.

6/ Violating stipulated in Sub-Article (3) of Article 64 of this Proclamation shall be punished with simple imprisonment not exceeding Three years or a fine of up to One Hundred Thousand Birr.

7/ Violating stipulated in Sub-Article (4) of Article 64 of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment not exceeding Seven years and a fine up to Five Hundred Thousand Birr.

8/ Found violating Sub-Article (1) of Article 65 of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment of up to Ten years.

9/ Found violating Sub-Article (2) of Article 65 of this Proclamation shall be punished with rigorous imprisonment of not less than Ten years.

PART TEN
Miscellaneous Provisions

68. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue Regulations to implement this Proclamation.

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ The Ministry may issue Directive necessary to implement this proclamation and the Regulations issued in accordance Sub-Article (1) of this Article.

፷፱. <u>የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

69. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

፩/ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፯፻፳፱/፪ሺ፬ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

1/ Sport Facilities Administration Proclamation No. 729/2011 hereby repealed.

፪/ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉት ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

2/ Any proclamation, Regulation, Directive or work procedure contrary to this proclamation shall not be applicable.

፸. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

70. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall be effective from the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

Done at Addis Ababa, On this 3rd day of July, 2026

TAYE ATSKE SELASSIE
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA